# የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደር ፍርድ ቤት መመስረት፣ ሥልጣን እና ተግባር ዳሰሳ

በቅርብ ዓመታት በኢትዮጵያ መንግስት በማክሮ ኢኮኖሚ ዘርፍ ከተወሰዱ ዋና ዋና እርምጃዎች እና ወደ ተግባር እየገቡ ካሉ የፋይናንስ እና የኢኮኖሚ ዘርፎች ማሻሻያዎች መካከል የካፒታል ገበያ ስርአትን እውን ማድረግ አንዱና ዋነኛው መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። የኢትዮጵያ

የካፒታል ገበያ ከበርካታ ጊዜያት ጥናት እና ዝግጅት በኋላ ሀምሌ 16 ቀን 2013 ዓ.ም አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ሆኖ በይፋ መታወጁ ይታወቃል።

የኢትየጵያ ካፒታል ገበያ ባለስልጣን በካፒታል ገበያ አዋጅ፣ በንግድ ሕግ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የሀገራችን የሕግ ማዕቀፎች ውስጥ የሚገኙ ከዓላማው እንዲሁም ከስልጣንና ተግባሩ ጋር የተገናኙ ዘርፈ ብዙ ኃላፊነቶች ተሰጥቶቷል። እነዚህን ተግባርና ኃላፊነቶቹን ለመወጣት ከቦርድ ጀምሮ ዋና ዳይሬክተር፣ ምክትል ዋና ዳይሬክተር እና ሌሎች አስፈላጊ ሰራተኞች ይዞ ተዋቅሯል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ከግብይቱ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ውሳኔዎችን የመስጠት ስልጣን ያለው ሲሆን ነገር ግን በገበያው ተሳታፊዎች ላይ የሚተላለፉ ውሳኔዎች ያለምንም ቅሬታ ተቀባይነት ያገኛሉ ወይም ምንም እንከን አይገኝባቸውም ማለት ግን አይደለም። ባለስልጣኑ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ቅር የተሰኙ ሰዎች ቅሬታቸው በይግባኝ እንዲታይላቸው የሚያስችል ስርዓት ያለ ሲሆን በአዋጁ ሰባተኛው ክፍል አንቀጽ 64 ስር የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምሮ የሚወስን ከመደበኛው ፍርድ ቤት የተለየ ህጋዊ ሰውነት ያለው አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ተቋቁሟል።

*"የአዋጁ አንቀጽ 65 አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በባለስልጣኑ ወይም የባለስልጣኑን ተግባርና ስልጣን በሚያስፈጽም ሰው በተላለፈ ውሳኔ ላይ የቀረበን ይግባኝ የመስማትና የመወሰን ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ይደነግጋል። "*

እነዚህ ቅሬታዎች ከመደበኛው የፍርድ ቤት አሰራር እና የክርክር ሂደት በተለየ የገበያውን ልዩ ሁኔታ ባማከለ መልኩ ከሕግ፣ ከንግድ ሥራ ወይም ከፋይናንስ ወይም ከሒሳብ አያያዝ፣ የሰነድ ሙዓለ ንዋይ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የተዋቀረ የዳኞች ስብስብ ተመርምሮ የባለሥልጣኑ ውሳኔ የሚፈተሸበት የዳኝነት አሰራር በአዋጁ ተዘርግቷል።

የአዋጁ አንቀጽ 65 አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በባለስልጣኑ ወይም የባለስልጣኑን ተግባርና ስልጣን በሚያስፈጽም ሰው በተላለፈ ውሳኔ ላይ የቀረበን ይግባኝ የመስማትና የመወሰን ስልጣን የተሰጠው መሆኑን ይደነግጋል። ከዚህ ደንጋጌ መገነዘብ የሚቻለው ባለስልጣኑ እንደአስፈላጊነቱ ለሌሎች አካላት ስልጣኑን በውክልና ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ነው። ይሄውም ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ማንኛውንም ስልጣን እና ተግባራት ለአንድ ለተለየ ተልዕኮ ለተቋቋመ ኮሚቴ፤ እውቅና ለተሰጠው ራሱን በራሱ ለሚቆጣጠር ድርጅት ወይም ለግለሰቦች በውክልና ሊያስተላልፍ እንደሚችል በአዋጅ አንቀጽ 16 ተደንግጓል። በመሆኑም ከባለስልጣኑ ውሳኔዎች በተጨማሪ እነዚህ የባለሥልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት በሚሰጡት ውሳኔ ቅሬታ የተሰማው ማንኛውም አካል ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የክርክር ሂደት የሚጀምረው ይግባኝ ባይ የሆነው አካል በካፒታል ገበያ ባለስልጣን ወይም የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት በተሰጣቸው አካላት በተላለፈበት ውሳኔ ላይ ውሳኔው በደረሰው 28/ሃያ ስምንት የሥራ ቀናት ውስጥ ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በሚያቀርበው የይግባኝ ቅሬታ ነው። የይግባኝ ባዩ ቅሬታ ከነዝርዝር ማስረጃው ለባለስልጣኑ እንዲደርሰው ተደርጎ ባለስልጣኑ በጉዳዩ ላይ መልስና ላስተላለፈው ውሳኔ መሠረት የሆኑትን ማስረጃዎች አባሪ አድርጎ በማቅረብ እና ችሎቱ ግራ ቀኙን በቃል በማከራከር፣ በመጠየቅና እንደ አግባብነቱ የሙያ ምስክር በመስማት ጉዳዩ በጥልቀት መርምሮ የሚደርስበት መደምደሚያ የአስተዳደር ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይሆናል።

የአዋጁ አንቀጽ 71(4) ባለስልጣኑ የይግባኝ ማስታወቂያው በደረሰው በ7 (ሰባት) የሥራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ከተጠየቀበት ጉዳይ ጋር ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን ቅጂ ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ መላክ አለበት በማለት ይደነግጋል። ይሁን እንጂ በሀገራችን ባሉ በሁሉም የአስተዳደር ፍርድ ቤቶች ባሉ እና የውጭ አገራት ተሞክሮ ጭምር የሚያሳዩት የካፒታል ገበያው በአስተዳደር ፍ/ቤቱ በመልስ ሰጭነት ተሰይሞ በቅሬታ አቅራቢው ላይ በባለስልጣን መ/ቤቱ የተላለፈው ውሳኔ ተገቢነት ላይ የፍሬ ነገር እና የሕግ መከራከሪያውን በማስረጃ አስደግፎ እንደሚያቀርብ እና አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ 73 ስር የተመለከተውን የይግባኝ ክርክር አሰማም ሂደት ይግባኝ ባዩን እና መልስ ሰጭ የሆነውን ባለስልጣን መ/ቤቱን የሚወክል አካል በተገኙበት የሚሰማ ይሆናል። አስተዳዳር ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ሰሚ እንደመሆኑ ሁሉንም ተከራካሪ ወገን ጠርቶ የመሰማት እድል መስጠት እና ማከራከር ትክክለኛ ውሳኔ ከመስጠት እና ፍትሕን ለማስፈን የሚያበረክቱት ሚና አንጻር ከፍተኛ መሆኑ ግልጽ ነው።

የካፒታል ገበያ ማቋቋሚያ አዋጁ የአስተዳደር ፍ/ቤቱን የውሳኔ አሰጣጥ ጊዜን በማሳጠር ረገድ እምርታ አሳይቷል። አዋጁ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥበትን ጊዜ በመደበኛነት 60/ስልሳ/ የሥራ ቀናት እንዲሆን በመደንገግ የሙግት ተካፋዮችን ገንዘብ፣ ጊዜ እና ጉልበት በሚቆጥብ መልኩ አፋጣኝ ፍትህ እንዲሰጥ ቁርጠኝነቱን የሚያሳይ ድንጋጌ አስፍሯል። ይህ የስልሳ ሥራ ቀናት ቀነ ገደብ በብዙ ጉዳዮች ላይ የሚስተዋለውን በመደበኛ እና በሌሎች አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡ ክርክሮችን ላልተወሰነ እና በውል ለማይታወቅ ጊዜ በማራዘም በተከራካሪ ወገኖች ላይ የሚያደርሰውን ዘርፈ ብዙ ጫና የሚቀንስና የሚያስቀር ነው። የአዋጁ አንቀጽ 73(2) አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ በተጠየቀ በ60(ስልሳ) ሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት በማለት በአስገዳጅነት ደንግጓል።

ይህ እንግዲህ በመርህ ደረጃ በአዋጅ በግልጽ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ላይ የተጣለ ኃላፊነት ሲሆን ይህንኑ በተግባር ለማዋል የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አመራር፣ ተሿሚ ዳኞቹ እና ሰራተኞች ጉዳዮችን በተቀላጠፈ መልኩ እልባት ለመስጠት በሚያስችል ቁመና ተደራጅቷል። የአዋጁ አንቀፅ 73(3) በልዩ ሁኔታ የጉዳዮችን ውስብስብነት ከግምት በማስገባት እና ለፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ሰብሳቢ የይግባኝ መወሰኛ ጊዜውን ከ30/ሰላሳ የሥራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው እንደሚችል ስልጣን ይሰጣል። ይህም ሲሆን ለተከራካሪ ወገኖች ስለጊዜው መራዘም የጽሑፍ ማሳወቂያ መስጠት ያስፈልጋል።

ይህ ውሳኔ የመስሚ ቀኑን ከ30/ሰላሳ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ የማራዘሙ ሂደት በጠባቡ ተተርጉሞ እንደ ሕጉ አነጋገር ውስብስብነት ባላቸው የይግባኝ ጉዳዮች ላይ ብቻ ተግባራዊ ሊደረግ የሚገባው ነው። አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የጽሑፍ፣ የቃል ክርክር እና ለጉዳዩ አስፈላጊ የሆኑትን ሰነዶች ከመረመረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል። በአዋጁ አንቀጽ 73(8) ስር በተደነገገው አግባብ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ለመወሰን ያበቁትን ምክንያቶች እንዱሁም ጥያቄ ባስነሱ ጭብጦች

ላይ የደረሰበትን ግኝት፣ የማስረጃውን ዋቢ ወይም ሌሎች ለግኝቱ መሠረት የሆኑ ፍሬ ነገሮችን ማካተት አለበት።

አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን ይግባኝ ከመረመረ በኋላ እንደ አግባብነቱ፦

ሀ) የመጀመሪያውን ትእዛዝ ወይም ውሳኔ እንዳለ ሊያፀናው፣ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው፤

ለ) አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ ነው ብሎ በወሰነው አግባብ ጉዳዩን እንደገና እንዲያየው ወደ ባለስልጣኑ ሊመልሰው፤ ወይም

ሐ) እራሱ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ ትክክለኛ ነው ብሎ የሚያምነውን ማናቸውም አይነት ሌላ ትእዛዝ ወይም ውሳኔ ሊሰጥ፤ እንሚችል በአዋጁ ሰፍሮ ይገኛል።

በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን በሕግ ረገድ ተፈጸመ የሚለውን ስህተት ለማሳረም ለፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ ይችላል። በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለመጠየቅ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 74 ወደ ፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ስለመጠየቅ በሚል ርዕስ በአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ተከራካሪ አካል ውሳኔውን ባወቀ በ30 (ሰላሳ) የሥራ ቀናት ውስጥ በህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል በማለት ደንግጓል ።

ከዚህ ጋር ተይይዞ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ የሚሰጠው ውሳኔ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደርሶ መጨረሻው ምን ይሆናል የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል። እንደ አዋጁ ድንጋጌ በፍሬ ነገር ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ነው። ይህ የፍሬ ነገር ጉዳይ ይግባኝ የሌለው ግራ ቀኙን የሚያስገድድ እና በሁሉም አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች በሚታዩ ጉዳዮች ተግባራዊ የሚደረግ ከሞላ ጎደል በሁሉም አካላት ስምምነት ያለው መርህ ሆኖ የቀጠለ ጉዳይ ነው።

ሌላው በዚህ አዋጅ ሊታይ የሚችለው ነገር የአዋጁ አንቀጽ 74 በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ይግባኝ የሚያቀርበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱን ውሳኔን በማጽናት፣ በመሻር ወይም በትዕዛዝ ወደ ስር ሊመልሰው ይችላል። ከአዋጁ አቀራረጽ እና መንፈስ የምንረዳው የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ላይ ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማይቀርብበት መሆኑን ነው። ሆኖም ይህ ማለት ግን ወደ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አይቀርብበትም ማለት አይደለም።

በኢፌዲሪ ሕግ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሐ)) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት ስልጣን ይኖረዋል በማለት ደንግጓል። በመሆኑም በክርክሩ ተካፋይ የሆነ ወገን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸሙን ጠቅሶ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ሕገ መንግስታዊ መብቱ የተጠበቀ ነው፡
፡

ይህ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስር ቅድመ ሁኔታዎች የተቀመጡለት ጉዳይ በመሆኑ በካፒታል ገበያ ጉዳይ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተቃውሞ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞብኛል በማለት የሰበር አቤቱታ የሚያቀርብ ወገን የዚህን አዋጅ መመዘኛ ማሟላቱን አረጋግጦ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

በአዋጁ አንቀጽ 71() እንደተመላከተው በካፒታል ገበያ ባለስልጣኑ ውሳኔ ላይ ለአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ የሚቀርበው ውሳኔው ከተገለፀለት በኋላ ባሉ 28 የሥራ ቀናት፣ በአንቀጽ ስር የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ለተከራካሪ ወገኖች የሚደርስበት/የሚገለጽበት አግባብ፣ በባለሥልጣኑ መ/ቤቱ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የሚያቀርብ

ወገን ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ስለሚከፈለው የዳኝነት ገንዘብ፣ በአንድ ችሎት ስለሚሰየሙ የዳኞች ብዛት እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን በተመለከተ አዋጁን ተከትለው በመዘጋጀት ላይ በሚገኘው የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት (Rules of Procedure) እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ የፍትሃብሔር ስነስርአት ህጉ መሰረት የሚወሰኑ እና የሚመሩ ይሆናል።

የካፒታል ገበያ አዋጅ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ አሰራሩን በተመለከተ በአንቀጽ 72 ባስፈረው ድንጋጌ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ ውሳኔውን፣ ብይኑን፣ ትእዛዙን እና የችሎት አካሄደን ለማስፈጸም በፍትሐብሔር ሥነ-ስርዓት ህግ ለመደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ስልጣን እንደሚኖረው ይደነግጋል። ይህ ድንጋጌ በበርካታ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ አፈጻጸማቸውን አስመልክቶ ባለጉዳዮችን ግራ ሲያጋባ እና በሕግ ባለሙያዎች መካከል ለልዩነት ምክንያት ሲሆን የነበረውን በአስተዳደር ፍርድ ቤት የሚሰጥ ውሳኔ መፈጸም የሚችለው በምንም መልኩ ነው የሚለውን ውዝግብ የሚያስቀር እና ለሌሎችም በምሳሌነት መጠቀስ የሚችል ድንጋጌ ነው።

ይህ በአፈጻጸም ጉዳይ ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ሰባተኛ መጽሐፍ ስለ ፍርድ አፈጻጸም የተደነገገው ድንጋጌ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ በሚሰጡ ውሳኔዎች አፈጻጸም ላይ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል። ይህም ማለት አስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱ የራሱንም ሆነ በራሱ ውሳኔ ላይ በይግባኝ ታይቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አልያም ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ውሳኔዎችን የአፈጻጸም አቤቱታ ሲቀርብለት በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የሰፈሩት አስገዳጅ ድንጋጌዎችን በመጠቀም እንደውሳኔው የማስፈጸም ስልጣን ተሰጥቶታል።

የካፒታል ገበያውንና በሰነድ ሙዓለ ንዋዮች ጉዳይ ጋር በተያያዘ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እና በተገልጋዩ መካከል ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን በዘርፉ የዕውቀትና ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ዳኝነት እንዲሰጥበት በሕጉ የተዘረጋውን ሂደት ካየን የዳኝነት ክፍሉን ዝግጅት ጠቁመን ለዛሬ ያዘጋጀነውን የካፒታል ገበያ የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤቱን ዳሰሳችንን እንቋጨለን። የካፒታል ገበያ ባለስልጣን እንዲሁም የሰነደ መዓለ ንዋይ ገበያው እራሳቸውን የማደራጀት ስራ አጠናቀው ወደ ትግበራ የተሸጋገሩ መሆኑን ተከትሎ አሁን ላይ የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤትም የአደረጃጀት ሂደቱን አጠናቆ በካፒታል ገበያ ዙሪያ የሚከሰቱ አለመግባባቶችን በይግባኝ ተቀብሎ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት የሚያስችለውን ዝግጅት አጠናቋል።